የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 72
ADDIS ABABA 25th July, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፱/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሩዋንዳ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገው የአሳልፎ መስጠት ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ........................................ገጽ ፲፪ሺ፯፻፳

## Content

Proclamation No.1219/2020

Extradition Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Rwanda Ratification Proclamation........................Page 12,720

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፱/፪ሺ፲፪

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሩዋንዳ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ መስጠት ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሩዋንዳ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ መስጠት ስምምነት ሚያዝያ ፳ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም. በኪጋሊ የተፈረመ በመሆኑ፤

ስምምነቱን ማፅደቅ ወንጀል ፈጽመው የኮበለሉ ግለሰቦችን ለፍርድ ለማቅረብ የሚያስችል በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባው ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION NO. 1219/2020

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE EXTRADITION AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF RWANDA

WHEREAS, the Extradition Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Rwanda has been signed in Kigali on the 28th day of April 2017;

WHEREAS, ratifying the Agreement enables to bring fugitives to justice;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on 25th day of June, 2020;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

፩. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሩዋንዳ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገው የአሳልፎ መስጠት ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፱/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **<u>ስምምነቱ ስለመፅደቁ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሩዋንዳ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ሚያዝያ ፳ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በኪጋሊ የተፈረመው የአሳልፎ መስጠት ስምምነት ፀድቋል፡፡

፫. **<u>የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ኃላፊነት</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱን የማስፈፀም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

፬. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ወ/ሮ ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Extradition Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Rwanda Ratification Proclamation No.1219/2020".

2. **<u>Ratification of the Agreement</u>**

The Extradition Agreement signed in Kigali on the 28th day of April, 2017 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Rwanda is hereby ratified.

3. **<u>Responsibility of the Attorney General</u>**

The Attorney General of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby authorized to follow up the implementation of the Agreement in collaboration with other government organs.

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force up on publication in the *Federal Negarit Gazette*.

**Done at Addis Ababa, on this 25th day of July, 2020**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**